Haile Selassie I - Harar Military Academy North America
ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሰሜን አሜሪካ

# *HSIHMAA Bimonthly Meeting News Bulletin*

የሁለት ወር  መደበኛ ስብሰባ ዜና

ቀን፦ ቅዳሜ፤ ኦገስት **23/2025**

የስብሰባ ቦታ:-

***6601 Little River Tnpk # 200***
***Alexandria, VA 22313***

የስብሰባ አዘጋጆች፤
ኮሎኔል ገበየሁ ኦስማንና ወይዘሮ የምስራች ደምሴ



የስብሰባ ሰዓት፦

ከ**1፡00-5፡00** ፒ.ኤም

የማህበሩ ስብሰባ በ2፡00 ሰዓት የተጀመረ ሲሆን ከምሳ በፊት በነበረው ፕሮግራም ከመካከላችን በሞት ለተለዩን አራት  አባላት የአንድ ደቂቃ ህሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል፦

*ሀ. ሜ/ጀኔራል መስፍን ገብረቃል (አካዳሚ አስተማሪ የነበሩና በተለያዩ የመከላከያ ሚንስቴር መ/ቤት በከፍተኛ ሃላፊነት ያገለገሉ)*

*ለ. ኮሎኔል መለስ ወልደዮሐንስ (6ኛ ኮርስ አባል)*

*ሐ. ሌ/ኮሎኔል ዮሐንስ መኮንን (13ኛ ኮርስ አባል)*

*መ. ሻለቃ ተሾመ ሸንቁጤ (17ኛ ኮርስ አባል)*

ከ**2፡00- 3፡00** ፒ. ኤም የምሳና የአባላት የግል ጊዜ ነበር።



ከ**3፡00-5፡00** ፒ. ኤም የአሉምናይ ማህበሩ አባላት በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ውሳኔ አሳልፈዋል።

- ሜይ **18** ቀን **2025** የተካሄደው መደበኛ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በንባብ ተሰምቶ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።
    - 
- የማህበሩ ገንዘብ ያዥ የማህበሩን ወርሃዊ የገንዘብ ሪፖርት ለጉባኤው አቅርበዋል።
    - 
- ቀጥሎ አባላት ተሻሽሎ በቀረበው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገዋል። መተዳደሪያ ደንቡን አሻሽለው ለውሳኔ እንዲያቀርቡ የተማረጡት ኮሎኔል ጎሹ ወልዴና ሻለቃ ሰለሞን ክፍሌ መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች አንቀጽ በአንቀጽ ለይተው ካቀረቡ በኋላ አባላት በጥልቀት ተወያይተው "የአሉምናይ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ" በሙሉ ድምጽ አጽድቀዋል። የጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተፈርሞ ለአባላት እንዲሰራጭ ወሳኔ ተላልፏል።

  በመቀጠልም ከአባላት መካከል በሕመምና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በማህበሩ ስብሰባ ላይ ሊገኙ ላልቻሉ አባላት ምን ይደረግ? የሚል ጥያቄና አስተያየት ከአባላት ተነስቶ ነበር። ጥያቄው በጣም አስፈልጊ መሆኑ ታምኖበት ግብታዊ ውሳኔ ከመተላለፉ በፊት ጥናት ተደርጎ ለውሳኔ ማቅረብ እንደ ሚገባ ከስምምነት ላይ ተደርሶ ጉዳዩን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አጥንቶ እንዲያቀርብ ተወስኗል። ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ብቻውን የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ ስለ ማይችል አባላት ያላቸውን አስተያየትና መፍትሔ ሃሳብ እንዲጠቁሙ በወቅቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

በእለቱ ስብሰባ ላይ  የተገኙ አባላት በከፊል






Maison Perrier


EXIT


코리안커뮤니티센터
K-COMMUNITY CENTER
HSI-HMA History and Mission Statement



በመጨረሻም የእለቱን መስተንግዶ በአስደሳች ሁኔታ ለአዘጋጁት የኮሎኔል ገበየሁ ኦስማንና የወይዘሮ ምስራች ደምሴ መላ ቤተሰብ ምስጋና ቀርቦ ስብሰባው በ5፡00 ፒ. ኤም ተጠናቋል።